የጃርዲያ ኢንፌክሽን በሽታ

የኢንፌክሽን መከላከያ ሀኪም የሚሠጥ የመረጃ ወረቀት: የበሽታ መረጃ

የጃርዲያ የኢንፌክሽን በሽታ ምንድነው?

ጃርዲያ: ተቅማጥ: ማቅለሽለሽና የሆድ መንፋት የሚያስከትል ያንጀት ጥገኛ ነፍስ ነው። በጃርዲያ የተለከፈ ሰው እስክኪታመም ድርስ ከ1-2 ሳምናታት ይወስዳል። ሰው ሳያውቅ በበሽታው ሊለከፍም ይችላ። በሽታው በጸረ-ተህዋስያን (ኣንቲቢዮቲካ) መፈወስ ይቻላል። ጃርዲያ ህክምና ካልተደረገለት በሰው አንጀት ለረጅም ጊዜ ሊቆይ ይችላል።

ሰው እንዴት በጃርዲያ በሽታ ይለከፋል፤ ወደ ሌላ ሰው እንዴት መተላለፍ ይችላል?

ኣብዛኛው ጊዜ የጃርዲያ በሽታ: በጥገኛ ነፍስ በተበከለ ምግብና መጠጥ ይተላለፋል። ጃርዲያ ሙቀት ስለ ስለሚገድለው: የተቀቀለ ወይ የተጠበሰ ምግብ በሽታ የማስተላለፍ አደጋ አያስከትልም። በሽታ የሚያስከትለው ጥግኛ ነፍስ ሰገራ ውስጥ ይገኛል፤ ከሰው ወደ ሰውም መተላለፍ ይችላል። በዚህም ምክንያት የእጅና የሽንት ቤት ጽዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ታላቁ በሽታ የመተላለፍ አደጋ ተቅማጥ ነው። የታመመው ሰው የጸረ-ተህዋስያን (ኣንቲቢዮቲካ) መድኃኒት የሚወስድ ከሆነ ግን አደጋው በተሎ ይቀንሳል። ኣብዛኛው ጊዜ ሰው ውጭ አገር ሲሄድ ነው በሽታው የሚለከፈው። ቢሆንም በሽታ በስዊድንም ሊተላለፍ ይችላል።

የሚከተሉትን መሪያዎችንና የጽዳት ምክሮችን በመከተል: የአንቲቢዮቲካ መድኃኒት የሚወስድ ሰው: ምንም የበሽታ ምልክት ሳይታይበት መሥራት ወይም ባፀደ ህፃናት መማር ይችላል።

ወደ ሌሎች በሽታ ላለማስተላለፍ ሊያስቡባቸው የሚገባዎት ነገሮ ምንድን ናቸው? መመሪያዎችና የጽዳት ምክሮች:-

- ተቅማጥ ከያዘዎት ወደ ሥራ መሄድ የለብዎትም።
- ሽንት ቤት ቆይተው መግብ ከመያዝዎና ከመመገብዎ በፊት እጅዎን በደምብ ይታጠቡ።
- ፈሳሽ ሳሙና: የግልዎ መወልወያ ወይም የወረቀት መወልወያ ይጠቀሙ።
- የሰገራው ወንበርና እጅ መታጠቢያ በጽዳት ይያዙ።
- የሽንት ጨርቅ (ብሎያ) የሚለብሱ ልጆች በበሽታው ከተጠቁ: የሽንት ጨርቁ ከቀየሩ በህዋላ እጅዎን በደንብ ይታጠቡ። የልጅ ልብስ መቀየሪያው ጠረጴዛም በጽዳት ይያዙ። የቆሸሸ የሽንት ጨርቅ በፕላስቲክ ተጠቅልሎ ይጣላል።
- ተቅማጡ ቆሞ ሰገራው እንደ ተለመደው ደረቅ ሆኖ አንድ ሳምንት እስኪያልፍ በመዋኛ/ገንዳ (ባሴንግ) መታጠብ የለብዎትም።

- ተቅማጥ የያዛቸው ልጆች ወደ አፀደ ህፃናት መሄድ የለባቸውም። ቢሆንም: የአንቲቢዮቲካ መድኃኒት ከወሰዱ በሁዋላ በተከታታይ የበሽታ ምልክታ ካላሣዩ ወደ አፀደ ህፃናቱ መመለስ ይችላሉ። በአፀደ ህፃናት የሚማሩ ልጆች: የአንቲቢዮቲካ ፍወሳ ከተደረገላቸው ከሦስት ሳምንት በህዋላ ምርመራ ይደረግላቸው።
- ሥራዎ ያልታሸጉ ምግቦችን የሚመለከት ከሆነ: በአውሮጳ የምግብ ህግ መሠረት የሥራ አለቃዎን የማሣወቅ ኃላፊነት ኣለዎት።

የጃርዲያ የኢንፌክሽን በሽታ: በስዊድን ኢንፌክሽን ህግ (smittskyddslagen) መሠረት: ለህብረተሰብ አደገኛ (allmänfarlig sjukdom) ተብለው ከሚታወቁት በሽታዎች አንዱ ነው። ስለሆነም ሀኪምዎ የሚሠጥዎትን ምክሮች የመከተልና የበሽታ ምንጭ ወይም ሌሎች ሰዎች ተለክፈው እንዳይሆን በሚደረገው ጥረት የመተባበር ግዴታ አለዎት።

በሚኖሩበት አውራጃ (län) ያለው የኢንፌክሽን መከላከያ ሀኪምን (smittskyddsläkaren): የተሠጠዎትን መመሪያ በድጋሚ እንዲያይ መጠየቅም ይችላሉ። ግምገማው እስኪገባደድ ድረስ ግን የተሠጠዎትን መመሪያ ይከተላሉ።